# የኢትዮ-ኪዩባን በሰሜን አሜሪካ መረበ-እድር ማቋቋሚያና መተዳደርያ ደንብ

## መተዳደርያ ደንብ

## Ethio-Cubans "Edir" in North America (USA-Canada) - Draft Bylaws

እኛ ኑሮአችን በሰሜን አሜሪካ የሆነ ኢትዮ-ኪዩባን ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ምክንያት በማድረግ በ.............፣.......፣ **2021** ይህ መረበ እድረ ተቋቁማል:: ለመቋቋሙ ዋና ዋና ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው

1. የዚህ እድር አስፈላጊነትና ዓላማ
   1.1. የቀብር ስነ ስርአት እቅድ ማውጣት አስፈላጊና ሁላችንም በአንድ ወቅት ላይ በህይወታችን ውስጥ የሚደርስብን ስለሆነ
   1.2. የቀብር ስነ ስርአትን ለማካሄድ የሚጠይቀው ዋጋ ውድና በየጊዜው የሚያጋጥመንና የሚያስቸግረን ጉዳይ ሆኖ ስለተገኘ
   1.3. የቀብር ስነ ስርአት የሚወጣውን ወጪ በስርዓት ለማስተዳደር በቅድሚያ እቅድ ማውጣት አስፈላጉ በመሆኑ
   1.4. የቀብር ስነ ስርአት የሚያስከትለውን ወጪ ለመጋራት መረዳዳትና መደጋገፍ ስላሰፈለገ
   1.5. ከልጅነት እስከ አውቀት ተፈቃቅረን እንደወንድም አህት በሄድንበት ሁሉ እንደኖርነው በሞት ስንለያይም ለቤተሰብ እንዲሁም ለቀባሪ ወንድሞቻችንን አይዞህ ባይና ለችግር ደራሽ መሆን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱና በሞት ግዜ የሚከሰቱ ችግሮችን ወጥ ባለው መልኩ ለመቅረፍ ይረዳ ዘን መመርያና ደንብ አውጥቶ ጠንካራ “የኢትዮ-ኪዩባን በአሜሪካ መረበ-እድር” መመስረት ስላስፈለገ ይህ መተዳደርያ ደንብ ተዘጋጅቷል።
2. ትርጉምና መግለጫ
   2.1. ኢትዮ-ኪዩባን በአሜሪካ (ኢ .ኪ .አ) ማለት በትውልድ ኢትዮጵያዊ (በአሁኑ ሰዓት ሌላ ዜጋነት ሊኖራቸው ይችላል) ሆነው ለትምህርት ኪዩባ የሄዱና በአሁኑ ሰዓት ኑራቸውን በሰሜን አሜሪካ ያደረጉ ማለት ነው።
   2.2. ኩባ የነበሩ መምህራን ማለት ኢትዮጵያን ወጣቶች ለማስተማር የሄዱና ቤተሰቦቻቸውን ማለት ነው
   2.3. ኢትዮ-ኪዩባን በአሜሪካ መረበ ማለት በሰሜን አሜሪካ ውስጥ በምናባዊ መንገድ የተዘረጋና በሞት ወቅት ለሚደርስ ችግር የተቋቋመ መረዳጃ ማህበር ማለት ነው። በሞት የሚደርስ ችግር የሚለው ሀረግ በመርዶ ጊዜ የሚደርስን ችግር አያካትትም
   2.4. ኢትዮ-ኪዩባን በአሜሪካ የመረበ እድሩ አባል ማለት፤ የመመዝገብያ ክፍያና ወርሀዊ ክፍያውን በተሰጠው የግዜ ገደብ ውስጥ ከፍሎ የተገኘ ወይም አባልነቱ የተረጋገጠ ማለት ነው፡፡
   2.5. የዕድሩ አባል ቤተሰብ ማለት የዕድሩ አባል በትዳር አጋርነት (ሚስት ወይም ባል) እንዲሁም ልጆች ብሎ የእድሩ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የእድሩ አባል በዝርዝር ያመሰገባቸው ሰዎች ማለት ነው።
   2.6. በአንድ የዕድር አባል ስር በተጠቃሚነት የሚመዘገቡ ቤተሰቦች ባል/ሚስት እና ልጆችን ብቻ የሚያካትት ነው። እናት፤ አባት ወንድም፤ እህትን አያካትትም
3. አንቀፅ **3.** የዕድሩ ስምና ፅፈት ቤት
   3.1. ስም፤ የዕድሩ ስም ኢትዮ-ኪዩባን በአሜሪካ መረበ እድር ((ኢ .ኪ .አ መረበ-ዕድር) በመባል ይታወቃል
   3.2. ፅፈት ቤት፡ የዕድሩ ፅፈት ቤት ምናባዊ ሆኖ መገናኛ መአከሉ የእድሩ ሊቀመንበር በሚገኙበት የሰሜን አሜሪካ ክፍለ-መንግስት ይሆናል
4. የመተዳደሪያ ደንቡ አላማ
   4.1. ይህ መተዳደርያ ደንብ የዕድሩ ዝርዝር አሰራር ማብራርያና ወይም መግለጫ ህጋዊ ሰነድ ሆኖ ያገለግላል
5. የመተዳደርያ ደንቡ አገልግሎት ስፋትና መጠን
   5.1. ይህ ደንብ የአባልነት ግዴታቸውን ለተወጡ የእድሩ አባላት፤ በአባላት ተመርጠው በሀላፊነት ለሚያገለግሉ ቦርድ አባላት፤ የስረ አመራር አባላት በሙሉ ያለ ልይነትና አድሎ ተፈፃሚ ወይም ተግባራዊ ይሆናል
6. አመሰራረት

6.1. ይህ ዕድር የተመሰረተው በትውልድ ኢትዮጵያዊ ሆነው ለትምህርት ኪዩባ የሄዱ፤ ቤተሰቦቻቸው እንዲሁም ወጣቶችን ለማስተማር ወደ ኩባ የሄዱ መምህራንና ቤተሰቦቻቸው በአሁኑ ሰዓት ኑራቸውን በሰሜን አሜሪካ ያደረጉ ግለሰቦች ነው

6.2. እንደ አስፈላጊነቱ በሌሎች ሀገሮች ቅርንጫፍ እድር ሊከፍት ይችላል

6.3. የዚህ እድር አመሰራረት በአሜሪካ አትራፊ ያልሆኑ ድርጅቶች በሚጠቀሙበት 501 (ሲ) 3 መሰረት ነው

**7.** ዓላማው

7.1. የዚህ ዕድር ዋንኛ ዓላማ በትውልድ ኢትዮጵያዊ ሆነው ለትምህርት ኪዩባ የሄዱና በአሁኑ ሰዓት ኑራቸውን በሰሜን አሜሪካ ያደረጉ እንዲሁም በቅፁ ላይ የተሞሉ የቤተሰብ አባላት ላይ የሞት አደጋ በደረሰ ግዜ ቀብር ለማስፈፀም፤

7.2. እንዲሁም የሞት አደጋ በተከሰተ ጊዜ ገንዘብ ማሰባሰብን ወይም ልመናን ለማስቀረት።

7.3. የእድሩ አባል እንዳይቸገርና አባላቱም የችግሩ ተካፋይ ለመሆናቸው መተዳደርያ ደንቡ በሚፈቅደው መሰረት የቀብር ማስፈፀምያ ወይም አስከሬኑ ወደ ሀገር ቤት ይሄድ እንደሆነ ወጭውን ለመሸፈን (ለማገዝ)።

7.4. በተጨማሪም ለአባላቱ የህይወት ዋስትና መግባት አስፈላጊነት በማስተማር ለቋሚ ዘመዶቻቸው፤ ልጆቻቸው ዘላቂ መፍትሄ እንዲኖር ማበረታታትን ያደርጋል

**8.** የእድሩ አባል መሆን የሚችሉ

8.1. ምንም ልዩነትን ሳያካትት በትውልድ ኢትዮጵያዊ (አሁን ሌላ ዜግነት ሊኖራቸው ይችላል) ሆነው ለትመህርት ኪዩባ የሄዱና በአሁኑ ሰዓት ኑራቸውን በሰሜን አሜሪካ ያደረጉና ቤተሰቦቻቸው እንዲሁም ከ26 አመት በላይ የሆኑ ልጆቻቸው በሙሉ ፍላጎት በተናጥል ወይም በቤተሰብ ደረጃ አባል መሆን ይችላሉ

8.2. እናት ወይም አባታቸው ኩባ የተማሩ፤ ባል ወይም ሚስት ኩባ የተማረ የሆኑ ግለሰቦች በፍላጎት የእድሩ አባል መሆን ይችላሉ

8.3. በመምህርነት ከኢትዮጵያ ወደ ኩባ ሄደው ያገለገሉ መምህራንና ቤተሰቦቻቸው አሁን ግን ኑራቸውን በሰሜን አሜሪካ ያደረጉ ግለሰቦች በፍላጎት አባል መሆን ይችላሉ

8.4. በአንቀፅ 8.1. ያለውን መስፈርት ማረጋገጫ (ኪዩባ ለመማራቸው ወይም ማስተማራቸው ማረጋገጫ) የሌላቸው በሶስት የኩባ ምሩቃን የተረጋገጠ የምስክርነት ማረጋገጫ ቃል አያይዘው ማቅረብ ይገባቸዋል

8.5. በቤተሰብ ደረጃ በዕድሩ ቅፅ ላይ ተሞልተው በአባል ስር የእድሩ ተጠቃሚ መሆን የሚችሉ

8.5.1. ባል ወይም ሚስት ወይም የጋብቻ ወረቀት ሳይኖር ነገር ግን አብሮ የሚኖር የኑሮ አጋር

8.5.2. ከ 26 አመት በታች የሆኑ ልጆቻቸው

8.5.3. ከ 26 አመት በላይ የሆኑ ነገርግን የሚታይም ወይም የማይታይ በሀኪም የተረጋገጠ አካላዊ ጉዳት ኖራቸው በቤተሰብ ላይ ጥገኛ ሆነው የሚኖሩ ልጆች

8.6. የቤተሰብ አስተዳዳሪው ዋናው የእድሩ አባል በሞት ቢለይ ከላይ በተደነገገው የእድሜ ክልል ውስጥ ያሉ በቅፁ ላይ የተሞሉ የቤተሰብ አባላት በአባልነት የእድሜ ክልሉ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ሊቀጥሉ ይችላሉ

8.7. የእድር አባልነት በውርስ አይተላለፍም

8.8. በቤተሰብ ደረጃ የእድር አባል የነበሩ ባልና ሚስት ወይም ጥምር የኑሮ ጓደኛ ቢለያዩ፤ በተናጥል ቅፅ ሞልተው 50% የመመዝገብያ ከፍያ እና ሙሉ ወርሀዊ ከፍያቸውን በመክፈል መቀጠል ይችላሉ።

8.9. የእድሩ አባል በአንቀፅ 2.4. ከተጠቀሱት አዲስ የቤተሰብ አባል ካለው ወይም ካላት ማስመዝገብ ይችላሉ ሆኖም ግን ይህ አዲስ የቤተሰብ አባል የዕድሩን ጥቅም ለማግኘት 180 (መቶ ሰማንያ) የመቆያ ቀናት መጠበቅ ግዴታ ነው።

**9.** ምዝገባ

9.1. በአንቀፅ 8 የተዘረዘረውን መስፈርት የሚያሟሉና የኢትዮ-ኪዩባን በአሜሪካ መረብ እድር አባል መሆን የሚፈልጉ ሁሉ በእድሩ መረብ-ገፅ ላይ የሚገኘውን ቅፅ በመሙላትና ከዚህ በታች የተዘረዘረውን የመመዝገበያ ሂሰብ ከፍለው መመዝገብ ይችላሉ

9.1.1. የእድሩ መመዝገብያ ክፍያ አባል ለመሆን የሚያመለክተው ግለሰብ በሚመዘገቡበት አመት እድሩ በሞት አደጋ ግዜ እንዲከፈል ከወሰነው አመታዊ ክፍያ በሙቶ አምስት እጁን (5% - አምስት %) መክፍል ይጠበቅበታል

9.1.2. ቤተሰብ ያላፈራ (በተናጥል) ወይም ባለቤተሰብ የእድር አባል መሆን የፈለገ ሰው የሚከፍለው የመመዝገብያውም ሆነ ወርሀዊ ክፍያው አንድ አይነት ነው

9.1.3. እድሩ በተቋቋመበት አመት (2021) በሞት አደጋ ግዜ የሚከፈለው $10000 (አስር ሺህ) እንዲሆን ስምምነት ላይ ስለተደረሰ የዚሁ አመት (2021) የእድር አባልነት መመዝገብያ $500 (አምስት መቶ) የአሜሪካን ዶላር (የ$10000 (አስር ሺህ) ዶላር 5%-አምስት %) እንዲሁም ወራዊ ክፍያ $20 የ6 ወር $120 (መቶ ሀያ) ($6*20= 120) በድምሩ $620.00 (ስድስት መቶ ሀያ) ነው

9.1.4. የእድር አባል የሆነ ሰው በአንቀፅ 8 ላይ የሰፈሩትን መስፈርቶች የሚያሟላ ማስረጃ ለእድሩ ስብሳቢ ማቅረብ ይጠበቅበታል። ያቀረበው ማስረጃ ተቀባይነት በወቅቱ ባሉ በእድሩ ሀላፊዎች ትክክለኛነቱ ተረጋግጦ እስካልተፈቀደለት ድረስ የእድሩ አባል የመሆን ወይም ጥቅም ማግኘት አይችልም

9.1.5. መስፈርቱን ያሟላና ተገቢውን ክፍያ ያጠናቀቀ ሰው የእድሩ ሀላፊዎች ማስረጃዎችን አጣርተው ተክክለኛነቱን ካረጋገጡበት 180 ቀን (6 ወር) ወደ ፊት ተቆጥሮ የእድሩን ሙሉ ጥቅም የማግኘት መብት ይኖረዋል።

9.1.6. የእድሩ አባል ለመሆን ያመለከተ ሰው በሞት አደጋ ግዜ ከእድሩ የሚገኘውን ጥቅም በሀላፊነት ተረክቦ ከእድሩ ሀላፊዎች ጋር የሚያሰፈፅመውን ሰው በቅፁ ላይ መሙላት ይጠበቅበታል

9.1.7. ማንኛውም የእድር አባል የተሳሳተ መረጃ በማቅረብ፤ በማጭበርበር፤ ገንዘብ የተቀበለ፤ ከእድሩ ጥቅም ያገኘ በህግ ተጠይቆ ገንዘቡን፤ የጠበቃና የፍርድ ቤት ወጪ እንዲሁም ተጓዳኝ ወጭዎችን እንዲሸፍንና ገንዘቡን ከነ ወለዱ እንዲመልስ ይደረጋል። ብሎም ከአባልነት ሙሉ በሙሉ ያለ ምንም ክፍያ ወይም ቀሪ ሂሳብ ይሰናበታል።

**10.** የአባልነት ክፍያና ግዴታ

10.1.1. ወርሀዊ መዋጮ በሁለት ግዜ ክፍያ በጥርና በሀምሌ (በፈረንጆቹ አቆጣጠር) ይካሄዳል

10.1.2. በ60 ቀናት ውስጥ ክፍያውን ሙሉ በሙሉ በባንክ አሰራር ብቻ እንዲከፈል ተደርጎ በተዘጋጀው የክፍያ መንገድ ማጠናቀቅ አለበት ።

10.1.3. አባላት ክፍያውን ወደ እድሩ የባንክ ሂሳብ ቁጥር በቀጥታ በዘመናዊ ወረቀት አልባ የገንዘብ የመላኪያ ዘዴዎችን በመጠቀም መክፈል ይጠበቅባቸዋል። በጥሬ ገንዘብ ወይም በቼክ መክፈል አይቻልም

10.1.4. በ60 ቀናት ወስጥ ያልከፈለ አባል በቀጣዮቹ 30 ቀናት ውስጥ 25% (ሃያ አምስት %) ጨምሮ እንዲከፍል ይደረጋል

10.1.5. ወርሀዊ ክፍያውን በተጠቀሰው ግዜ ገደብ ያልከፈለ ሰው በሚያዚያና በጥቅምት ላይ በሚደረገው የሂሳብ የማጣራት ስራ ወቅት ከአባልነቱ ሙሉ ለሙሉ እንዲሰናበት ይደረጋል። ተመልሶ ለመግባትም ከፈለገ እንደ አዲስ የመመዝገብያ ክፍያ እንዲያደርግ ይጠየቃል።

**11.** የአባልነት ጥቅም

11.1. የእድሩ አባል በሞት በተለየ ጊዜ ለቀብር ማስፈፀምያ እንዲረዳ አስር ሺ የአሜሮካ ዶላር ($10000) ይከፈላል። ይህ የገንዘብ መጠን በያመቱ የአድሩ አቅም፣ የአገልግሎት ወይም ገበያው ሁኔታ እተመረመረ ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል

11.2. የእድሩ አባል የሚጠበቅበትን ክፍያ በተሰጠው የግዜ ገደብ (60 ቀን) ውስጥ ሳይከፍል የሞት አደጋ ቢያጋጥም ከሚከፈለው ሂሳብ ላይ 10% ተቀንሶ ቀሪው ይከፈለዋል

11.3. የእድሩ አባል በሞት ሲለይ በእድሩ ቅፅ ላይ የተሞላው ተወካይ አስፈላጊ የሆኑትን ማስረጃዎች (የሞት ማረጋገጫ፤ የሟች እንዲሁም የተወካዩ መታወቅያ ፤ የእድሩ ቅፆችን ) አሟልቶ ማቅረብ አለበት

11.4. የእድሩ አባል በሞት ሲለይ በከተማው ያሉ የእድሩ አባላት ተገኝተው ይቀብራሉ ወይም ወደ አገር ቤት የሚሄድ ከሆነ ይሸኛሉ፤ ቤተሰብን ተገኝተው ያፅናናሉ

11.5. በእድር አባል ስር የተመዘገበ/ች የቤተሰብ አባል በሞት ከተለየ ባለሙብቱ አስፈላጊ የሆኑትን ማስረጃዎች (የሞት ማረጋገጫ፤ የሟች እንዲሁም የተወካዩ መታወቅያ ፤ የእድሩ ቅፆችን ) አሟልቶ ማቅረብ አለበት

11.6. በአንዳንድ ምክንያቶች የሞት ማረጋገጫው የማይደርስ ከሆነ ቤተሰብ ከእድሩ ሀላፊዎች ጋር በመነጋገር አስፈላጊው ክፍያ በቀጥታ ለቀብር አስፈፃሚው ድርጅት እንዲከፈል ማስደረግ ይችላል።

11.7. እድሩ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በማስረጃዎች ላይ ክፍያውን ከማድረጉ በፊት ከ7 ቀን ባልበለጠ ግዜ ውስጥ ማጣራት እንዲሁም ተጨማሪ መረጃ የመጠየቅ መብቱ የተጠበቀ ነው

11.8. አጠራጣሪ በሆኑ ጉዳዮች ተጨማሪ ማስረጃ ካስፈለገ የእድሩ ባለመበት ከተጠየቀበት ቀን ጀምሮ በ7 ቀናት ውስጥ ማቅረብ ይኖረበታል

**12.** የእድሩ አባላት መብት

12.1. አባላት በሁሉም ምርጫ የመሳተፍ፤ የመምረጥ፤ የመመረጥ፤ ሀሳብ የመስጠት ሀላፊነት አለባቸው or መብት አላቸው

12.2. አባላት በእድሩ አባላት ከተመረጡ በማንኛውም የእድሩ አመራር ክፍል ገብተው ማገልገል ይችላሉ

**13.** የእድሩ አባላት ግዴታ

13.1. መተዳደርያ ደንቡን ሙሉ በሙሉ ማክበር

13.2. የአባልነት መዋጮን በወቅቱ መክፈል

13.3. የቤተሰብ አባልትን ማስመዝገብ፤ ለውጥ ሲኖርም መረጃቸውን አቅረበው የእድሩን ቅፅ መሙላት

13.4. በግንባርም ሆነ በመረበ-ምናብ በሚደረጉ ስብሰባዎች መሳተፍ

13.5. ለሀላፊነት ወይም ለተሳትፎ እድሩ በጠየቀው ግዜ በሙሉ ፍላጎት ማገልገል

**14.** የእድሩ መገናኛ ዘዴዎች

14.1. ዋናው የእድሩ መገናኛ ዘዴ በቪርቹዋል መረበ-ምናብ ወይም መረበ-ስልክ ይሆናል

14.2. ሁኔታዎች ከፈቀዱ አመራር ቦርዱ በመረጠው አማካኝ ቦታ በግንባር መገናኘት ይቻላል

**15.** የእድር አባል ስንብት

15.1. የአባልነት ክፍያውን በተሰጠው የግዜ ገደብ (60ቀን) ውስጥ ያላጠናቀቀ

15.2. በራሱ ፍላጎት ከአባልነት መሰናበት ከፈለገ በፅሁፍ ካሳወቀበት ቀን ጀምሮ አባልነቱ ይሰረዛል

15.3. በማንኛውም መልኩ ከእድሩ የሚሰናበት ሰው የከፈለው ገንዘብ አይመለስለትም

**16.** የእድሩ አደረጃጀትና ሀላፊነት

16.1. የኢትዮ-ኪዩባን በሰሜን አሜሪካ መረበ ዕድር **(**ኢ.ኪ.እ**)** ጠቅላላ ጉባኤ

16.1.1. የኢትዮ-ኪዩባን በአሜሪካ ጠቅላላ ጉባኤ፤ የመረበ ዕድሩ አባላት በሙሉ በግንባር ወይም በቪርቹዋል በመረብ፤ በስልክ የሚገኙብት ስብሰባ ማለት ነው።

16.1.2. .የእድሩ የበላይ ተጠሪ አካል ጠቅላላ ጉባኤው ነው

16.1.3. ጠቅላላ ጉባኤው ሁሉን የእድሩን አባላት የሚያጠቃልል ነው

16.1.4. ጠቅላላ ጉባኤው የእድሩን አመራር አካላት በየሁለት አመቱ ይመርጣል

16.1.5. ጠቅላላ ጉባኤው መተዳደርያ ደንቡን ያፀድቃል፤ ያሻሽላል

16.1.6. አመታዊ የገንዘብ ወጪን ገቢን እንዲሁም በሞት ግዜ የሚከፈለውን ክፍያ እንዲሁም ወርሀዊ ክፍያን ያሻሽላል፤ ያፀድቃል

**16.2.** የእድሩ ቦርድ አመራር አካል

16.2.1. ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤው ነው

16.2.2. የቦርዱ አባላት ቁጥር ከሶስት ያልበለጠ ነው

16.2.3. ቦርዱ ከጠቅላላ ጉባኤው ቀጥሎ የኢ. ኪ. እ በአሜሪካ የበላይ አካል ነው

16.2.4. እንደ አሰፈላጊነቱ መተዳደሪያ ደንቡን ማሻሻያ ሀሳቦች ለጠቅላላ ጉባኤ አቅርቦ በአባላት ውሳኔ እንዲያገኝ ያደርጋል

16.2.5. የእድሩን የሂሳብ እንቅስቃሴ ከእድሩ የስራ አመራር ጋር በመሆን በየስድሰት ወሩ ምርመራ ያስደርጋል ውጤቱን አመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ያቀርባል

16.2.6. የቦርዱ ሊቀመንበር ከእድሩ የስራ አመራር አካል ጋር በመሆን የእድሩን አመታዊና የእለት ወጪ ባጀትን ያፀድቃል

16.2.7. የእድሩን ደንብና ስርዓት አፈፃፀምና ተግባራዊነት ይከታተላል እንደ አሰፈላጊነቱም የእርምት አርምጃ ይወስዳል።

**16.3.** የስራ አመራር አካል

16.3.1. ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤው ነው

16.3.2. አምስት አባላት ይኖሩታል

16.3.3. የስራ ዘመኑ ለሁለት አመት ግዜ ነው

16.3.4. አንድ ተመራጭ በእድሩ አባላት ምርጫ ከሁለት ግዜ በላይ ማገልገል አይችልም። ሆኖም ሁለት ጊዜ አገልግሎ ከአንድ አመት ቆይታ በኋላ በድጋሚ መመረጥ ይችላል።

16.3.5. በጠቅላላ ጉባኤው የተመረጡ ሊቀመንበር፤ ምክትል ሊቀመንበር፤ ፀሀፊ፤ ገንዘብ ያዥ፤ ሂሳብ ሹም ይኖሩታል

16.3.6. በመተዳደርያ ደንቡ መሰረት  የእድሩን እቅድ ያሰፈፅማል፤ ገቢና ወጪን ሆነ እለት ተእለት ስራዎችን ያከናውናል

16.3.7. የእድሩን የስራ እንቅስቃሴ፤ ገቢና ወጪ ዘገባ በየስድስት ወሩ ያዘጋጃል

16.3.8. በአመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ በዝርዝር ገቢና ወጪን ሂሳብ ዘገባ ያቀርባል

16.3.9. የእድሩን አመታዊ ባጀትና ስራ ማስካሄጃ ሂሳብ በጠቅላላ ጉባኤ ያስወስናል። ስራ ማስካሄጃው ለስልክ፤ ኢንተርኔት አገልግሎት የሚወጣውን ያካትታል

16.3.10. አመታዊ ስብሰባን ያቀናጃል (መረበ-ምናብ፤ መረበ-ስልክ ወይም በግንባር ከመረበ ምናብ ጋር የተጣመረ)፤

16.3.11. እንደ አሰፈላጊነቱ ከቦርዱ አባላት ጋር በመነጋገር አስቸኳይ የጠቅላላ ጉባኤ ጥሪ ማድረግ ይችላል

16.3.12. የእድሩ አባላት 25% (ሃያ አምስት %) በፅሁፍ ልዩ ስብሰባ ይጠራልን ብለው ከጠየቁ የመወያያ መድረክ አማራጮቹን በመጠቀም ስብሰባውም የመጥራትና የመምራት ግዴታ አለበት

16.3.13. የእድሩን አባላት ለጠቅላላ ጉባኤ ከሁለት ሳምንት በፊት ጥሪ ያደርጋል በኢሜል ወይም በፅሁፍ መልክት ያስታውቃል ፤ ከስብሰባው 24 ሰዓት ቀደም ብሎ የመጨረሻ ጥሪ በኢሜል ያስተላልፋል

16.3.14. የእድር አባል ሲሞት በትክክልና በወቅቱ የሚከፈለው ክፍያ መፈፀሙን ያረጋግጣል

16.3.15. የእድሩ የገንዘብ አቅም አነስተኛ ሆኖ ሲገኝና የገጠመ ችግር ካለ፤ የሥራ አመራር ከቦርዱ ጋር በመገናኘት ከአባላት ተጨማሪ መዋጮ ተሰብስቦ እንዲሸፈን ያስደርጋል

16.3.16. እድሩ የሚያድግበትን እንዲሁም በሌሎች ክፍለ አህጉር ወይም ሀገር በተለይ ኢትዮጵያ ካሉ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ጋር አብሮ በትብብር የሚሰራበትን መንገዶችን አጥንቶ ዝርዝሩን ለጠቅላላ ጉባዔ በማቅረብ ያፀድቃል ተግባራዊም ያደርጋል

16.3.17. እንደ አሰፈላጊነቱ የሚመረጡ ወይም የሚወከሉ ከየክፍለ መንግሰቱ (እስቴት) ተጠሪነታቸው ለስራ አመራሩ የሆኑ ተወካያ አባላትን ያስመርጣል

- 16.3.17.1. የክፍለ መንግስት (እስቴት) ተወካይ
  - 16.3.17.1.1.1. የእድሩ አባል በሞት ሲለይ በከተማው ያሉ የእድሩ አባላት ተገኝተው እንዲቀብሩ ወይም ወደ አገር ቤት የሚሄድ ከሆነ እንዲሸኙ ያሰተባብራል
  - 16.3.17.1.1.2. በቀብር ስነ ስርአቱ ላይ እድሩን በመወከል የአበባ ጉንጉን ያሰቀምጣል
  - 16.3.17.1.1.3. ለቀብር ስነሰራቱ የህይወት ታሪክ ዝግጅት፤ ለሶሰት ቀን የሚሆን መስተንግዶ ከቤተሰብ ጋር እየተነጋገረ ዝርዝር የስራ እቅድ በማውጣት ያስፈፅማል
  - 16.3.17.1.1.4. ለአበባ ጉንጉንና ድንገተኛ ወጭ እስከ $500 ከእድሩ ሂሳብ ወጪ የሚደረግበትን ከስራ አመራር አካል ጋር በመመካከር አግባብ ባለው መልኩ ወጪ አድርጎ ደረሰኞቹን ለሂሳብ ሹሙ ይልካል፤ ያወራርዳል።
  - 16.3.17.1.1.5. አዲስ አባላትን ሰለ እድሩ አላማ በማስገንዘብ እንዲመዘገቡ ያሰተባብራል
  - 16.3.17.1.1.6. አባላት ክፍያቸውን እንዲፈፅሙና ግዴታቸውን እንዲወጡ ያነቃቃል።
  - 16.3.17.1.1.7. በስራ አማራር ስብሰባ ላይ በመሳተፍ ስለ ክፍለ መንግሰቱ (እስቴት) ዘገባ ያቀርባል
  - 16.3.17.1.1.8. አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የስራ አመራሩ ሊቀመንበር ወይም ምክትል ሊቀመንበር ከወከላቸው በአቅሪያባቸው በሚደረግ አንዳንድ መሄበራዊ ስብሰባዎች ላይ እድሩን ወክለው ሊገኙ ይችላሉ።

16.3.18. የስራ አመራሩ ሊቀመንበር ወይም ሰብሳቢ

- 16.3.18.1. የስራ አመራሩን ስብሰባዎች በሊቀመንበርነት ይመራል
- 16.3.18.2. የእድሩ የባንክ ሂሳብ ወጪ ወይም ገቢ ሰነዶች ላይ ከእድሩ ገንዘብ ያዥ ጋር በጥምር ይፈርማል
- 16.3.18.3. እድሩን በመወከል አሰፈላጊ በሆኑ ስብሰባዎች ላይ ይገኛል

16.3.19. ምክትል ሰብሳቢ

- 16.3.19.1. የእድሩ ሊቀመንበር በሌለበት ተክቶ ይሰራል፤ ሰነዶች ላይ ይፈርማል
- 16.3.19.2. እንደ አሰፈላጊነቱ ሊቀመንበሩ የሚሰጠውን የስራ ሀላፊነት ያከናውናል

16.3.20. ፀሀፊ

16.3.20.1. የስብሰባ አጀንዳዎችን ያዘጋጃል።
16.3.20.2. ቃለ ጉባኤዎችን ይይዛል ያዘጋጃል በስብሰባው ለተገኙት አባላት ዘገባዎችን አዘጋጅቶ ያሰራጫል
16.3.20.3. የእድሩ አባላት ዝርዝርና ወርሀዊ የባንክ ሂሳብ በእድሩ ምናበ ገፅ ላይ ይደረጋል
16.3.20.4. ለአባላት የስብሰባ ጥሪ በስልክ፤ በፁሁፍ ያስተላልፋል። የተገኙትንም ይመዘግባል

16.3.21. ገንዘብ ያዥ
16.3.21.1. የእድሩን የባንክ ሂሳብ ከስራ አመራሩ ሊቀመንበር ጋር በመሆን ይከፍታል
16.3.21.2. ወርሀዊ ክፍያንም ሆኖ የመመዝገብያ ክፍያን በትክክል ወደ ባንክ ሂሳቡ መግባቱን ያረጋግጣል
16.3.21.3. የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ያቀርባል
16.3.21.4. አመታዊ የስራ ማስካሄጃ ባጀትን ያዘጋጃል አቅርቦም ያፀድቃል

16.3.22. ሂሳብ ሹም

16.3.23.
16.3.23.1. የገንዘብ ወጪን ገቢን እንዲሁም በሞት ግዜ የሚከፈለውን ክፍያ ይፈርማል ይፈፅማል። ለተጠቃሚዎቹ እንዲደርስ ያደርጋል
16.3.23.2. የሂሳብ ሪፖርትን አዘጋጅቶ ያቀርባል

**16.4.** የቁጥጥር ኮሚቴ እና የሥራ ሃላፊነት

**16.4.1.** አባላቱ ከሁለት ያልበለጡ ናቸው
**16.4.2.** ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤው ነው
**16.4.3.** የእድሩን የገንዘብ አስተዳደርና አያያዝ ወጪና ገቢ እንቅስቃሴ ይመረምራል
**16.4.4.** አመታዊ ዘገባ ለጠቅላላ ጉባኤው ያቀርባል
**16.4.5.** አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ወቅትና ቀን አስቸኳይ የሂሳብ ምርመራ ሊያደርግ ይችላል
**16.4.6.** አዲስ የእድር አመራር ሲተካ ማንኛውንም የሂሳብ ዘገባና ሰነድ ለተተኪው ክፍል ያቀርባል

**17.** ስብሰባና የድምፅ አሰጣጥ ስነስርአቶች

17.1. መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ
17.1.1. በዓመት አንድ ግዜ አመቺ በሆነ መልኩ ተዘጋጅቶ ይከናወናል
17.1.2. የስብሰባው ቀንና ሰዓት እንዲሁም የሚካሄድበት መንገድ ከሁለት ሳምንት በፊት ለአባላት ይገለፃል በተደጋጋሚም ማስታወሻ በመላክ እንዲያውቁት ይደረጋል

**17.2.** ልዩ ጠቅላላ ጉባኤ
17.2.1. የእድሩ ቦርድ አባላት ወይም ስራ አመራር በአብዛኛው ድምፅ ወይም 25% (ሃያ አምስት %) የእድር አባላቱ በፅሁፍ በፊርማ የተረጋገጠ ጥያቂ ሲያቀርቡ ስብሰባው ሊጠራ ይችላል

**17.3.** የድምፅ አሰጣጥ ስነ ስርዓት
17.3.1. እያንዳንዱ አባል አንድ ድምፅ ብቻ ይኖረዋል

17.4. ለውሳኔ የሚቀርቡ ሀሳቦች፤ የደንብ ለውጦች 25% (ሃያ አምስት %) ወይም ከዚያ በላይ የእድሩ አባላት በተገኙበት ስብሰባ ላይ ብቻ ይሆናል። የቀረበው ሀሳብ ወይም ለውጥ ሊፀና የሚችለው በስበሰባው ላይ የተገኙት በአብላጫ ድምፅ ሲያፀድቁት ብቻ ነው።

17.5. ሁለት ግዜ ሰብሰባ ተጠርቶ ምልአተ ጉባዔው ካልተሟላ ከግማሽ ወይም ከዚያ በላይ የእድሩ ቦርድና ስራ አመራር አባላት ተገኝተው ያፀደቁት ሀሳብ የፀና ይሆናል

**18.** የእድሩ አደረጃጀት አስመራጭ ክፍል

18.1. ሶስት (3) አባላት ያሉት ነው

18.2. የቦርድ አባላቱና ስራ አመራሩ በጋራ ስብሰባ 50% (ሀምሳ %) የተገኙበት የሚመረጡ ናቸው

18.3. አስመራጭ ኮሚቴው የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ከእድሩ አባላት ጥቆማ ተቀብሎ ማጣራትን ያደርጋል፤ ብቁ ናቸው ያላቸውን ለውድድር ያቀርባል

18.4. የስራውን ተከታታይነት ለማረጋገጥ ሲባል፤ በአንድ የምርጫ ወቅት የቦርድና የስራ አመራር አባላት ሊተኩ የሚችሉት ሁለት ሶሰተኛው ብቻ ናቸው። ቀሪዎቹ አንድ ሶስተኛ አባላት አገልግሎታቸውን ከአዲስ ተመራጮች ጋር በመቀጠል በቀጣዩ ዙር ምርጫ በሌሎች ይተካሉ።

18.5. ምርጫው ትክክለኛና ህግ የተከተለ መሆኑን ያረጋግጣል

18.6. ለምርጫ ሄደት የተጠቀመባቸውን መረጃዎች ለእድሩ ስራ አመራር ያስረክባል

18.7. በአስመራጭነት የቀረበ ሰዎች በወቅቱ ለሚደረገው የእድሩ ለተለያዩ ሀላፊነት ቦታዎች ራሳቸውን እጩ አድረገው ማቅረብም ሆነ መመረጥ አይችልም

**19.** እድሩን ስለማፍረስ

19.1. ይህ እድር በማንኛውም ሰዓት 75% (ሰባ አምስት %) ወይም ከዚያ በላይ አባላቱ ተገኝተው እድሩን አላስፈላጊነት ተወያይተው እንዲፈርስ ከወሰኑና በስብሰባው ላይ የተገኙት ከ75% (ሰባ አምስት %) ወይም ከዚያ በላይ ድምፅ ሰጥተው ካፀደቁት ሊፈርስ ይችላል

19.2. እድሩ እንዲፈርስ ከተወሰነ በእድሩ ስም የሚገኝ ተንቀሳቃሽም ሆነ የማይንቀሳቀስ ሀብት ተሸጦ እንዲሁም በባንክ የሚገኘው ጥሬ ገንዘብ ሙሉ በሙሉ ለበጎ አድራጎት ስራ እንዲውል ለኢትዮጵያ ቀይ መስቀል መሀበር እንዲተላለፍ ይደረጋል። ይህንንም በወቅቱ ያሉት የቦርድ ሊቀመንበርና የስራ አመራር ሊቀመንበር አስፈፅመው ውጤቱን ለአባላቱ በማስረጃ አስደግፈው ለእያንዳንዱ አባል ይልካሉ።